## *የኦሮሞና የሲዳማ ወጣቶች ንቅናቄ የጋራ የኣቋዋም መግለጫ*

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ጭቁን ብሄር ብሄረሰቦች ለዘመናት ከተጫነባቸው የጭቆና ኣገዛዝ ቀንበር ለመላቀቅ ያልተቋዋረጠ ትግል ሲያካሄዱ ከዛሬ ደርሰዋል። የኦሮሞና የሲዳማ ህዝቦችም ሆነ ሌሎች ተመሳሳይ እጣ የገጠማቸው ብሄር ብሄረሰቦች ከፍተኛ የህይወትና የንብረት መስዋእትነት እየከፈሉ ለነጻነታቸው መረጋገጥ እየታገሉ ይገኛሉ። በዚሁ መሰረት እኛ የኦሮሞና የሲዳማ ወጣቶች በተለያዩ ጊዜያት እየተገናኘን በህዝቦቻችን የጭቆና ህይወት ዙሪያ ሲንወያይ ከቆየን በሁዋላ ከጥቅምት 24-26, 2012 ሲዳማ ዞን ውስጥ ያካሄድነውን ታሪካዊ ስብሰባ በስኬት ኣጠናቀናል። በዚህ ስብሰባ መሰረትም እኛ የኦሮሞ ወጣቶች ንቅናቄና የሲዳማ ወጣቶች ንቅናቄ የወያኔ መንግስት ጨቋዋኝ ስርኣት መሆኑን በመገንዘብ ጠንካራ የሁለትዮሽ ግንኙነት ፈጥረን ልንዋጋው ተዘጋጅተናል። ከጀግኖች ኣባቶቻችን የተረከብነውን የነጻነት ትግል በጋራ በማፋፋም የሃገራችንና የህዝቦቻችንን ነጻነት እውን ለማድረግ ቁርጠኛ ኣቋዋም መውሰዳችንን እነሆ ስናውጅ ከፍ ያለ ደስታ ይሰማናል። ባካሄድነው የጋራ ስብሰባ ላይ ሰፋ ያለ ውይይት ካካሄድን በሁዋላ የሚከተሉትን 8 ነጥቦች ያቀፈ የኣቋዋም መግለጫ ኣውጥተናል።

1. ቀንደኛው ጠላታችን የወያኔ መንግስት መሆኑን በመረዳት የትግል ኣንድነታችንን ኣጠናክረን ጠላትን በጋራ በመፋለም የሃገራችንና የህዝቦቻችንን ነጻነት እውን ኣናደርጋለን።
2. በትግሉ ሂደት ማንኛውም ኣይነት ችግር ወንድም የኦሮሞ ህዝብም ሆነ ወንድም የሲዳማ ህዝብን በሚያጋጥምበት ጊዜ በጋራ ተረባርበን ችግሮቹን በመፍታት የጋራ ኣላማችንን ከግቡ ለማድረስ በቁርጠኝነት እንሰራለን።
3. በሃገሪቷ ውስጥ በኣምባገነኑ የወያኔ መንግስት የታፈነው የጭቁን ህዝቦች ድምጽ ከኣፈና ተላቅቆ ለኣለም ማህበረሰብ ይሰማ ዘንድ በጋራ እንታገላለን።
4. እንደኛ ሁሉ ተመሳሳይ የኣፈናና የጭቆና እጣ ገፈት ቀማሽ የሆኑ ሌሎች ተጨቋዋኝ ህዝቦችንም ከጎናችን በማሰለፍ የትግል ክንዳችንን ኣስተባብረን በጋራ እንንቀሳቀሳለን።
5. በኦሮምያና በሲዳማ ኣካባቢዎች ሁሉ የህዝቦቻችንን የጸረ ጭቆና ኣመጽ ይበልጥ በማስፋፋት የወያኔ ስርኣትን መፈናፈኛ እናሳጣለን፣ የኣገዛዝ መዋቅሮቹንም እንበጣጥሳለን።
6. ሃገራችንና መላው ህዝቦቻችን ነጻነታቸውን እስከሚያረጋግጡ ድረስ ወንድ ሴት፣ ልጅ ኣዋቂ፣ ተማሪ ኣስተማሪ፣ ሰራተኛ ገበሬ ሳንል የመላውን ዜጎቻችን የፖለቲካ ንቃተ ህሊና ለማዳበርና ለትግሉ ለማሰለፍ ተግተን እንሰራለን።
7. ህዝብ ለመንግስት ያለውን ተቃውሞና በኣጸፋው መንግስት የህዝብን ተቃውሞ ለማፈን ሲል የሚወስዳቸውን ፋሺስታዊ የፈሪ እርምጃዎች በየወቅቱ በማጋለጥ የኣለም ማህበረሰብን ትኩረት እንዲስብ እንደርጋለን።
8. የሁለትዮሽ ግንኙነታችንን በይበልጥ ለማጠናከር የገባነውን ቃል ኪዳን ጠብቀን የኦሮሞና የሲዳማ ህዝቦችን እንዲሁም ሌሎች መሰል የተገፉ ህዝቦችን ነጻ ለማውጣት እስከመጨረሻው በቁርጠኝነት እንታገላለን።

እነዚህን የኣቋዋም ነጥቦቻችንን ወደ ተግባር ለመተርጎምም ከጊዜ ወደ ጊዜ ግንኙነታችንን እያጠናከርን ኣምባገነኑን የወያኔ መንግስት ኣስወግዶ የነጻነት ተስፋ ሊፈነጥቅ የሚችል የጋራ ትግል እንደምናፋፍም ከስምምነት ደርሰናል።

**ጭቁን ህዝቦች የራሳቸውን እድል በራስ ለመወሰን የሚያደርጉትን ትግል ያፋፍማሉ!**

**የኦሮሞ ወጣቶች ንቅናቄ**
**እና**
**የሲዳማ ወጣቶች ንቅናቄ**

**ጥቅምት 26 ቀን 2012**